★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ.41 ቁጥር 7 ሚያዚያ 2008 ዓ.ም

# ሕዝባዊ አመጹ ተጠናክሮ ግቡን እንዲመታ ድክመቶቻችንን እናርም

ባለፉት ጥቂት ወራት በአገራችን በተከታታይ የተካሄዱት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በዓይነታቸው በስፋታቸው በክብደታቸውና በሌሎች መለኪያዎች ለየት ያሉ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። ከደቡብ እስከ ሰሜን ከምሥራቅ እስከምዕራብ የአገራችንን ክፍል አዳርሰዋል። በጎንደር፣ በጎጃም፣ በወለጋ፣ በሸዋ፣ በከፋ፣ በኢሉባበር፣ በሐረር፣ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሲዳሞ፣ በጎማ ጎፋ፣ በወሎ፣ ... ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። የተለያዩ ብሔረሰብ አባላትም የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት በወያኔ አምባገነን አገዛዝ ላይ አመጽ አካሂደዋል። በወልቃይት የሚኖሩት የአማራ ብሔረሰብ አባላት የማንነት ጥያቄ አንስተዋል፤ ከኢትዮጵያ ግዛት ቆርሶ ወያኔ ለሱዳን መሬት መስጠቱን በመቃወም የትጥቅ አመጽ አካሂዷል፤ ቅማንትና አማራ መለያየት አለባቸው በማለት በሕዝብ መካከል ክፍፍል ለመፍጠር በወያኔ የተጎነጎነው ሴራም በትግል እንዲከሽፍ ተደርጓል። የኦሮሞው ብሔረሰብም የወያኔ ባለሥልጣናት በአዲስ አበባ ክልል መስፋፋት ሳቢያ ከአርሶ አደሩ ላይ መሬት ለመንጠቅ ያደረጉትን ሙከራ ለማክሸፍ ከፍተኛና ተከታታይ የሆኑ የአመጽ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። በተለያዩ ቦታዎች ወጣትና ሽማግሌ፣ ሴት ወንድ ሳይሉ መብታቸውን ለማስከበር ከፍተኛ ትግል አካሂደው፤ በርካታ መሥዋዕትነትን ከፍለዋል። የጋምቤላ ሕዝብ መሬቱን በወያኔ ለባዕዳን መቸብቸቡን በመቃወም ሲያካሂዳቸው የነበሩት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ባለፉት ወራት ተጠናክረው ቀጥለዋል። በደቡብ ጎሙጎፋ የኮንሶ ሕዝብ ለማንነት ያደረገው እንቅስቃሴም የህይወት ዋጋን አስከፍሏል።

በእነዚህ ወራት የታየው የሕዝብ እምቢተኝነትና አመጽ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች በተሰማሩት ለፍቶ አዳሪዎች ፣ በተማሪዎችና በተለያዩ እምነት ተከታዮች የተካሄዱትንም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች አካቷል። ዘርና ሃይማኖት እንዲሁም ክልል ሳይለያቸው በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የታክሲና የባጃጅ ሹፌሮችና ባለንብረቶች የወያኔን አፋኝ መመሪያ በመቃወም የሥራ ማቆም አድማ አድርገዋል፤ መምህራን ለደሞዝ ጭማሪ ሥራ አቁመዋል፤ የዩኒቨርሲቲና የሌሎች ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በተለያየ ወቅት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት የአመጽ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል። ነጋዴዎች የሚደርስባቸውን መረን የለቀቀ ገፈፋና አድሎዎን በመቃውም የሥራ ማቆም አድማ አድርገዋል። የተለያዩ እምነት ተከታዮችም ከወያኔ አፋኝ አገዛዝ ጋር እያካሄዱ ያለው ትግል ምንም እንኳ ካለፉት ጊዜያት ደከም ያለ ቢሆንም ሳይገታ መቀጠሉ ተስተውሏል። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ አባላት ለሃይማኖት ነጻነትና እኩልነት የሚያካሂዱት ትግል በተለያዩ መንገዶች ሲገፋበት፣ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምዕመናንም ቤተ ክርስቲያኗን ከወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ለማስወጣት የሚያካሂዱት ትግልም እንዲሁ በተለያየ መልክ ቀጥሏል።

የሕዝባዊ እንቅስቃሴዎቹ መነሻ ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆኑም መሠረታዊ ምክንያታቸው ግን አንድ ነው። የወያኔ አምባገነንና ጨቋኝ አገዛዝ የሚያካሄደው በደልና ግፍ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ መፍሰሱ ነው። ከእንቅስቃሴው ዓይነትና ካካተታቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ስፋት አንጻር ሲታይ በሀገራችን የፖሊቲካ ሥርዓት ላይ ጉልህ ለውጥ

እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ካደረገው ከየካቲት 66-ቱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም በጥልቀትና በግለቱ እንዲሁም ተከታታይነትን አግኝቶ በፖሊቲካ ሥርዓቱ ላይ ተጨባጭ ለውጥን ከ ማስገኘት አ ን ጻ ር ልዩነት ያለ መሆኑ በገሃድ የሚታይ ነው። በየአካባቢው የተከሰቱት አመጾች እንደ የካቲቱ አብዮት የገዥውን ክፍል ጎራ አሸብረዋል፤ ለአንዳንድ ሕዝባዊ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ አድርገዋል። እንደየካቲቱ አብዮት ወቅት የገዥው ክፍል አባላት ለሕዝቡ ጥያቄዎች ተንበርክከዋል። አልገዛም ባይነት በሰፊው ታይቷል፤ መንገዶች ተዘግተዋል፤ የገዥው ክፍል በባለቤትነት የሚቆጣጠራቸው ንብረቶቹ የወደሙበትንም አይተናል። በየአካባቢው የወያኔ መዋቅሮች ተሰባብረዋል፤ አስተዳዳሪዎች ከየአካባቢው ተባረው በሕዝባዊ አስተዳደሮች ተተክተዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች የወያኔ አገልጋይ የሆኑ ወታደሮችና የአካባቢው ኃላፊዎች ሰልፋቸውን ከሕዝብ ጋር አድርገዋል።

ይህ የታፈነ የሕዝብ ብሶትና ንዴት ገንፍሎ የወጣበት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የዜጎችን መስሥዋእትነትም ጠይቋል። ኦሮሞዎች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ቢያንስ ከ200 በላይ የሆኑ ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ከዚያ በላይ የሚሆኑ አካለ ስንኩላን ሆነዋል። በ10 ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች ታፍነው፣ ታስረዋል። በጎንደርም ወሰናችን ለሱዳን መስጠቱን በመቃወም በተንቀሳቀሱት ዜጎቻችን ላይ ወያኔ በወሰደው የጥቃት እርምጃ በርካታ ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ተይዘው ታስረዋል። በወልቃይት የማንነት ጥያቄ የጠየቁ ዜጎች ታፈነው ቀርተዋል። የቅማንቱን ማኅበረሰብ ከአማራው ለመለየት ወያኔ ያደረገው የተንኮል ሥራ በታጋይ ዜጎች ብርታት ሊከሽፍ ቢችልም ጉዳት ሳያስከትል አላለፈም። ባለፉት ወራት የተከሰቱት እንቅስቃሴዎች በደልና ጭቆና የወለዳቸው ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ይሁን እንጅ እንደ የካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንደቋያ እሳት ተቀጣጥለው ግለቱን ማያያዝ አልቻሉም። በእንቅስቃሴው ከፍተኛ ሽብርና ብርክ ይዟቸው የነበሩትና እስካሁን ያላገገሙት የወያኔ መሪዎች እሳቱ ተቀጣጥሎ እንዳያጠፋቸው ከወሰዱት የጭፍጨፋ እርምጃ ጎን ለጎን የተለያዩ የማጭበርበር እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል። የሕዝብን ጥያቄ መልሰናል ለማለት በኦሮሞው አካባቢ ለነበረው የአመጽ እንቅስቃሴ መነሻ የሆነውን የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ሽረናል ብለው በግድያው ላይ በሰፊው የተሰማሩት የወያኔው አግአዚ ኃይል አባላት ለፍርድ ሳያቀርቡ በደፈናው ለግድያው ይቅርታ ይደረግልን በሚል በይፋ በዜና ማሰራጫዎች ይቅርታ ጠይቀዋል። የራሳቸውን አባላት ለመቅጣት ሞክረናል ለማለትም ተገደዋል። ለሱዳን የተሰጠውን መሬት በሚመለከት ከሱዳን ጋር ስለወሰን ጉዳይ ድርድር የሚባል ነገር አልነበረም ብለው በአዳባባይ ሽመጥጠዋል፤ የወልቃይት ሕዝብን የማንነት ጥያቄ ውሃ በመቸለስ ለማቀዝቀዝ ሞክረዋል፤ የታክሲ ነጅዎች፤ የአስተማሪዎችና የነጋዴዎችን ጥያቄዎች በለሆሳስ ለማቀዝቀዝ ጥረዋል። ይህም በመሆኑ በአንድ በኩል የአስከፊው ቡድን አግአዚ ኃይሎች በወሰዱት የኃይልና የጭካኔ እርምጃ በሌላ በኩል ባለስሥልጣኖቹ ባካሄዱት የማጭበርበር የማታለልና የከፋፍል ሴራዎችና ተግባሮች እንቅስቃሴውን ከውስጥ ተብትበው በመያዛቸው ትግሉ ተያያዥነትና ተከታታይነት አግኝቶ ተጠናክሮ ሊቀጥል አልቻለም።

ሕዝባዊ አመጹ የቀዘቀዘ ቢመስልም ተዳፈነ እንጅ አልጠፋም። ለጊዜው አሸለበ እንጅ አልሞተም። ነገ ተነገ ወዲያ በአዲስ አዳዲስ ጥያቄዎች በስፋትና በጥልቀት እንደገና ተቀጣጥሎ እንደሚጀምር ጥርጥር የሚነሳበት አይደለም። እንደ የካቲት 66ቱ ሕዝባዊ አመጽ በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ለማስወገድ እንዲችል እና ከሥርዓቱ መወገድ በኋላ ሊመጣ የሚችለውን አስከፊ ሁኔታ ለመከላከል ግን የእንቅስቃሴውን ድክመትና ጉድለት ገምግሞ ተገቢውን ዕርማት መስጠትና መፍትሔውን መጠቆም ያስፈልጋል። በዚህ የዴሞክራሲያ ዕትም ለመጠቆም የምንሞክረው በእኛ በኩል የሚታየንን ግምገማና ለወደፊቱ ሊበጅ የሚችለውን የመፍትሔ ሀሳብ ነው።

በየቦታው ተከስተው የነበሩት ሕዝባዊ አመጾች እያንዳንዳቸው ልዩ የሆነ ጠባይ የነበራቸው ከመሆኑ የተነሳ ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም የአብዛኞቹን ጉድለቶችና ድክመቶች በአጠቃላይ መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል። የእንቅስቃሴው የዓላማ ጥራት መደብዘዝ ለድክመቱ እንደምክንያት ከሚጠቀሱት መካከል አንደኛው ነው። በየቦታው የነበሩት አመጾች መነሻ ምክንያታቸው የተለያየ ቢሆንም ዋነኛና መሠረታዊ የሆነው ምክንያት የወያኔ አገዛዝ በደልና ስቃይ

መሆኑ እየታወቀ እንቅስቃሴዎቹ የወያኔ አገዛዝን በማስወገድ ላይ የተቃኙ አልነበረም። አገዛዙ በሁኔታው በመደናገጥ ሕዝቡ ላነሳቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ተገዶ መልስ ሲሰጥ እንቅስቃሴዎቹ ቀዝቀዘዋል። በአንዳንድ ቦታዎች አዳዲስ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገው የተነሱ አመጾች ቢኖሩም ብዙም ሊገፉ አለመቻላቸውም ተስተውሏል።

የእንቅስቃሴው ሌላው ጉድለት የተያያዘና አገር አቀፍ አለመሆኑ ነው። በአንድ አካባቢ የተነሳው እንቅስቃሴ በሌላ አካባቢ ባለ ሕዝብ ተደግፎና ተጠናክሮ አልቀጠለም። በእንቅስቃሴው ወቅት የተንጸባረቁት አቋሞች ሌላውን የኅብረተሰብ ክፍል በአመጹ እንዲሳተፍ የሚጋብዙ ሳይሆን እንዲያውም ከመተባበር የሚያርቁ ሆነው ተገኝተዋል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ስም የመሬት ዝርፊያ ለማካሄድ የታቀደውን ሴራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊቃወም፤ ሊታገልለትና ሊሞትለት ይገባ ነበር። ከተማ ማሳደግ በሚል ፈሊጥ ደኻውንና ጭቁኑን አርሶ አደር ከመሬቱ ላይ ለማፈናቀልና ለማባረር የተጠነሰሰው ሴራ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚቆጠቁጥ ደሙን ሊያፈስለት የሚገባ የትግል ዘርፍ ነበር። ይሁን እንጅ ውዥንብር መልክቶችን የቀላቀሉ መፈክሮች በመሰማታቸው አልፎም ፍራቻንና ስጋትን የሚያነግሱ እንቅስቃሴዎች በመደረጋቸው ሌሎች ወገኖች በትግሉ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን አልቻሉም። "የኦሮሚያ መሬት ለኦሮሞ ብቻ ነው" "ኦሮሚያ ለኦሮሞ ናት" የሚለው የጠባቦች መፈክር የሌሎች ብሔርና ብሔረሰብ አባላትን ከትብብሩ እንዲርቁ አድርጓል። ለረጅም ዘመናት ዓላማቸው ያልተሳካላቸው ጠባብና ከፋፋይ ድርጅቶች የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለመንጠቅ ባደረጉት እንቅስቃሴና ወያኔ የሚያካሄደው ስውር የሆነ የመከፋፈል ሴራ ተጨምሮበት የውዥንብሩ ደረጃ በጣም ጎልቶ ከፍ እንዲል በመደረጉ ሰፊው ሕዝብ በወገኑ በኦሮሞ ብሔረሰብ ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ ቢቆጠቁጠውምና ተቃውሞውን በየአደባባዩ ቢገልጽም በተግባር ከወገኑ ጎን ቆሞና ተባባሪ ሆኖ ትግሉን መቀጠል አልቻለም። ጥያቄው የሁሉም ዜጋ፤ በደሉም በሁሉም ዜጋ ላይ የደረሰ መሆኑ እየታወቀ ለራሳቸው ውስን ዓላማም ሆነ በቅጥረኛነት ተገዝተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ጥቂት ጠባቦች በጋራ ትግሉ ላይ እንቅፋት ፈጥረዋል። በጎንደር ክፍለሀገር ወያኔ ድንበራችንን ለሱዳን እንዳያስረክብ ግብ ግብ የገጠሙትና በወልቃይት የጎንደር መሬት ወደ ትግራይ በጉልበት መጠቃለሉን የተቃወሙት፤ ቅማንት አማራ የሚለውን የወያኔን የዘር ክፍፍል የተጋተሩት ወገኖች ከወያኔ ጋር ግብ ግብ ሲገጥሙ በሚፈለገው ደረጃ ሌላው ወገን ከጎናቸው ተሰልፎ አልታገለም።

ሌላው ድክመት እንቅስቃሴው ተገቢውን አመራር ለማግኘት አለመቻሉ ነው። አንዳንድ ክፍሎች የሕዝባዊ አመጹን ከሚያካሂዱት ጋር የግንኙነት ሰንሰለት የነበራቸው መሆኑ ግልጽ የነበረ ቢሆንም እንቅስቃሴውን በጥንቃቄ ያደራጀ፤ የተደራጀውንም አቀነባብሮ የመራ አካል እንዳልነበር ይታያል። ከሩቁ እናቀነባብራለን የሚሉ ክፍሎችም ራሳቸው የዓላማ ጥራት የጎደላቸው የሕዝባቸውን ፍላጎትና ጥቅም የማያውቁ፤ በመሬት ካለው እውነታ ጋር የተራራቁ በመሆናቸው በነበራችው ውሱን ግንኙነት እንኳ የበለጠ ውዥንብር ከመንዛት በስተቀር እንቅስቃሴው ተጠናክሮ እንዲወጣና የመጨረሻውን ግብ እንዲይዝ አላስቻሉትም።

ወያኔ በሥልጣን ላይ ከተቆናጠጠ ጀምሮ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ ቦታዎች የተካሄዱ ሕዝባዊ አመጾችና እንቅስቃሴዎች ለአገሪቷ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ በማስገኘት በኩል ድክመት ታይቶባቸዋል። ጥንካሬን የተላበሱ ሕዝባዊ አመጾች የወያኔ ዘረኛና አምባገነን አገዛዝን ማስወገድ እንዲችሉና ህልውናዋና አንድነቷ በተጠበቀ አገራችን ውስጥ ሕዝባችን የተሚላና ያልተሸራረፈ መብቱ የሚጠበቅበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት እንዲችሉ መሠረታዊ ድክመቶቻቸውን ማስወገድና ማረም ያስፈልጋል።

የመጀመሪያው እርምጃ የአመጹ ባለቤት የሆነው ወገን በአገር ሉዓላዊነትና በሕዝብ አንድነት ፤ በግላዊ ወይም በቡድናዊ ጥቅም ተያዥነት፤ እንዲሁም በመደራጀት አስፈላጊነት ላይ ግልጽ እና ጥርት ያለ አቋምና ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ነው። የአገራችን አንደነትና ሉዓላዊነት ካልተጠበቀ ብዙ የምንመኘለትና የምንጓጓለት ህልም እውን እንደማይሆን ግልጽ ነው። የብሔር እና የብሔረሰብ መብትና እኩልነትን ለማስጠበቅ የሚካሄድ እንቅስቃሴ፤

ለሃይማኖት ነጻነት የሚደረገው ትግል፤ ወይም ለተወሰነ የሙያ የቡድን ...ወዘተ ጥቅም የሚደረግ የሥራ ማቆም አድማም ሆነ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እይታቸውን ከአገርና ከሕዝብ አንድነት ከነጠሉ የተነሱበትን ግብ ለመምታት የማይችሉ ከመሆናቸውም በላይ ሕዝቡን ለማያቋርጥ ብጥብጥና ጦርነት ይዳርጋሉ። ለቡድን ሆነ ለግለሰብ መብቶች የሚደረጉ ትግሎች የአገርንና የሕዝብን አንድነት እስካልተጻረሩ ድረስ ሁሉም በትግሉ ሊሳተፍ እና ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገባ ነው። ኢትዮጵያ አገራችን የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ በርካታ ብሔረሰብና ብሔሮች እንዲሁም የተለያዩ የሃይማኖት እምነት ተከታዮች፤ ለረዥም ዘመናት በአንድ ላይ የኖሩባትና የጋራ ታሪክ የመሰረቱባት አገር በመሆኗ አንዱ ሲጠቃ፤ የአንዱ መብት ሲገፈፍ፤ አንዱ ጥቅሙ ሲገደብ ሌላውንም የሚመለከት በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ተከላካይ በመሆን መታገል ይገባዋል። ኦሮሞው ሲበደል አማራው ጉራጌው ትግሬው ሊደርስለት እንደሚገባው ሁሉ ሙስሊሙ ሲጎዳ ክርስቲያኑ ከጎኑ ሆኖ ቢዋደቅለት መልካም ይሆናል። የአንዱ መብት መገፈፍ፤ የአንዱ መጨቆን የሌላው ስለሆነ። ይሁን እንጅ የመብትም ሆነ የእኩልነት ጥያቄ አግባብነት የሚኖረውና የሚሰምረው የሕዝብ አንድነትና የአገሪቱ ሉዓላዊነት ጥያቄ ውስጥ ሳይገቡ ነው።

ከዚሁ ተያይዞ መገለጽ ያለበት ማንኛውም የሕዝብ ጥያቄና ችግር በየትኛውም የአመጽ መልክ ግቡን ለመምታትም ሆነ መፍትሔ ለማግኘት የሚችለው ዒላማውን በአገዛዙ ላይ ሲያዞር ብቻ መሆኑን ነው። ጨቋኙ አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ ሕዝብን የመብት ባለቤት የሚያደርግ ሥርዓት ሳይመሠረት በመካከል የሚገኝ መፍትሔ የይስሙላ ከመሆን አያልፍም። ለአንዱ መፍትሔ ቢገኝም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በሌላ መተካቱ አይቀርም። ለአንድ ጉዳይ የተሰጠ መልስም ሁሉንም የመብት ጥያቄ የሚመልስ አይሆንም። ስለሆነም ሕዝባዊ አመጹ የወያኔን አገዛዝ በማስወገድ ላይ ብቻ መቃኘት ይኖርበታል። የሀገሪቱ መሠረታዊ ችግር እራሱ ወያኔ ነውና !

የአመጹ ባለቤት የሆነው ዜጋ መገንዘብ የሚኖርበት ሌላው ዐቢይ ጉዳይ መደራጀት ወሳኝ መሆኑን ነው። በተገቢው መንገድ ሳይደራጅ በተናጠል የሚካሄድ እንቅስቃሴ በርካታ ብርቅዬ ዜጎች ህይወታቸውን ከሰጡ በኋላ በአገዛዙ የጸጥታ ኃይል በቀላሉ ተመትቶ የሚበታተን ይሆናል። በተናጠል የሚካሄድ አመጽ ለጥያቄ በገኘው ክፍል በሚሰጥ መልክ ወዲያውኑ ይፈታል። ያልተደራጀ አመጽ ለረጅም ጊዜ ፈተናዎችንና ውጣውረዶችን መክቶና ተወጥቶ ወደ ድል ለመሄድ አያስችለውም። ስለሆነም ዜጎች መሥዋዕትነት የሚከፍሉበት ትግል ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው ባመቻቸው መንገድ ተደራጅተው ሲታገሉ ብቻ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

ታጋዩን ሕዝብ ተገቢውን የዓላማና የትግል ዘይቤ ለማስጨበጥና አደራጅቶ ለማታገል በቅድሚያ ኃላፊነት የተጫነባቸው በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ መልኮች የተደራጁት የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው። በዚህ በኩል በርካታዎቹ ከፍተኛ ድክመት አሳይተዋል። አንዳንዶቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ለትግሉ እንቅፋት የሆኑትን ከማስወገድ ይልቅ ለችግሮቹ መከሰትና ምንጭ ከመሆን ጀምሮ ለመባባሳቸው ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም። ከደሙ ንጹህ ነን በሚል ራሳችንን ከድክመቱ ነጻ ሳናወጣ ዛሬ የፖሊቲካ ድርጅት ነን በሚሉት ላይ የሚታዩት ጎላ ያሉ ድክመቶች መታረም ያለባቸው ይመስለናል። ስም እየጠቀሱ ስህተት መጠንቀሉ አግባብ መስሎ ባይታየንም በጥቅሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ያለባቸውን ድክመት ማንሳታችን ችግሩ ተወግዶ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲወጣ ካለን ቅን ፍላጎት እንጅ ለመወነጃጀልና ለመካሰስ እንዲሁም ያልሆነ ንትርክ ለመፍጠር አለመሆኑን እንዲታወቅልን እንፈልጋለን።

በአገራችን የተለያዩ ቋንቋዎችን በሚናገሩ የተላያዩ ባህሎችና እምነቶች ባሏቸው ብሔርና ብሔረሰቦች መካከል የተለያየ የአስተሳሰብ ልዩነቶች ቢከሰቱና እነዚህም ልዩነቶች ለተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የተደላደለ ሁኔታ ቢፈጥሩ ብዙ የሚያስገርምም የሚያሳስብም አይደለም። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የተለያዩ የፖሊቲካ ድርጅቶች መኖራቸው ጠቃሚ እንጅ ጎጅ ሊሆን አይችልም፤ ለእድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ክስተት እንጅ እድገትን የሚጎትት አይደለም። ስለሆነም በአመለካከት፣ በፖለቲካ ፕሮግራም ...ወዘተ የተለያዩ በርከት ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸውን በደስታ

መቀበል የሚገባን ክስተት ነው።

ግለሰቦች ተሰብስበው የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያቋቁሙት ለኅብረተሰቡ ይጠቅማሉ ብለው የሚያምኑባቸውን የሶሻል የፖሊቲካ እና የኢኮኖሚ ፕሮግራምና ፖሊሲዎች ተግባራዊ ለማድረግ በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን ለመያዝ ቢሆንም አምባገነን አገዛዝ ሰፍኖ ባለበት ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅቶች ቀዳሚ ሚና አምባገነናዊ አገዛዝን ለማስወገድ መታገል ነው። ይህ እውን ሆኖ ሳለ ሁኔታውን በጥልቀት ባለመገንዘብ ወይም ሌላ አጀንዳ ለማራመድ ሲንቀሳቀሱ የሚታዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ።

በብሔር ብሔረሰብ ስም የተደራጁት ድርጅቶች ብሔር ብሔረሰቦች መብታቸው እንዲከበርና እኩልነታቸው እንዲጠበቅ የሚያካሄዱት ትግል የሚደገፍ ቢሆንም መገንጠልን ዋና አጀንዳ አድርገው በመንቀሳቀሳቸው የወያኔ ቡድን በሥስልጣኑ ኮርቻ ላይ ተደላድሎ ለረጅም ዘመናት እንዲቀመጥ ምክንያት ሆነው ቆይተዋል። ለዓመታት አብሮ በመኖር አገሪቷን የገነቡትንና ከውጭ ጠላት በመከካለከል ህልውናዋን ጠብቀው የኖሩትንና በሺ ክሮች የተሳሰሩትን ብሔርና ብሔረሰቦች ለመነጣጠል መሞከርን በመሬት ላይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ባለመፍቀዱ ይኸው በዚህ መልክ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ድርጅቶች ዓላማቸው እስካሁን ያልተሳካ ከመሆኑ ሌላ ድርጅቶቻቸውም የተዳከሙበት ወይም ቢያንስ የነበራቸው የጥንካሬ ደረጃ የቀነሰበት ሁኔታ ይታያል። በሌላ በኩልም የወኔንን አገዛዝ ለመገርሰስ ሲካሄዱ የነበሩትን ትግሎች ያዳከሙ ከመሆናቸው ሌላ ለገዥው ቡድን የፍራቻ ፕሮፓጋንዳ ጉዝጓዝ ሆነው ቆየተዋል። በዚህ በኩል መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው ድርጅቶቹ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድተውና ይዘውት የቆዩትን አቋም ገምግመው ድክመታቸውን ሲያስወግዱና ትክክለኛና ሊሆን የሚችል አቋም ሲይዙ ነው። የኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና እስከተጠበቀ ድረስ ማንኛቸውም ልዩነት በሕዝብ ውሳኔ ሊፈታ የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ዋና ዓላማቸው መገንጠል ከሆኑት ሌላ በአገሪቱ አንድነት መጠበቅና በሉዓላዊነቷ መከበር ላይ እምነት አለን የሚሉ ኅብረ ብሔርም ሆነ የብሔር ድርጅቶች ላይም የሚታይ ድክመት አለ። በወያኔ ውስጥ ሕጋዊ ፈቃድ አግኝተው ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ላለፉት 24 ዓመታት ሲከተሉት የነበረው የትግል ስልት አለመሥራቱንና እንቅስቃሴያቸው ህልውናቸውን እየተፈታተነና የወያኔን አገዛዝ እየጠቀመ መሄዱን መረዳት ይኖርባቸዋል። ሕጋዊ መድረክን ተጠቅሞ ሰላማዊ ትግሉን (ሰላማዊ የትግል ስልትን ተጠቅሞ) ማካሄድ ተገቢ ቢሆንም በየአምስት ዓመቱ በወያኔ የምርጫ ቲያትር መሳተፍ ወያኔን በቁንጅና "ከማሳመር " ውጭ ዋጋ ቢስ መሆኑን ያለፉት የ25 ዓመታት ተመክሮ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል። በስልትና በቆራጥነት ከተካሄደ ሰላማዊ ትግል የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ይችላል። ይሁን እንጅ ሰላማዊ ትግል ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል ቆራጥነትን፣ ጥንቃቄንም፤ ስልትንና ጽናትን የሚጠይቅ የትግል ስልት ነው። ሰላማዊ ትግልን የሚያካሂዱ ድርጅቶች የተለያዩ የትግልና የአደረጃጀት ስልትን መከተል አለባቸው። በምርጫ መሳተፍ ለሽፋን የሚደረግ ተግባራቸው ቢሆንም ግምባር ቀደም ዓላማ አድርገው መንቀሳቀስ ያለባቸው የወያኔ አምባገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት እንዲወገድና የሕዝብ ሙብት የሚጠበቅበትና የሚረጋገጥበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን መሆን አለበት። ለዚህም ለመሥስዋእትነት የተዘጋጁ መሪዎች ያስፈልጓቸዋል። አባሎቻቸውን በይፋ ማስመዝገብ ግድ ቢልም እነዚህ በትግሉ ወቅት በወያኔ ጥቃት ሲደርስባቸው ትግሉን በህቡዕ ሊያስቀጥሉ የሚችሉ አባላት ማደራጀት ይኖርባቸዋል። ይህ በሌለበት ሊከተል የሚችለው የወያኔ ጥቃት ነው። ሊሆን የሚችለው ለወያኔ ሰርጎ ገቦች ተጋልጦ መዳከምና መፈራረስ ነው። ካለፈው የአገራችን ተመክሮ የምንገነዘበው ይህንኑ ነው።

በወያኔ እገዳ ምክንያት ይፋ እንቅስቃሴዎችን በውጭ ለማድረግ የተገደዱ ድርጅቶች በውጭ አገሮች ከሚያካሂዱት የፕሮፓጋንዳ የዲፕሎማሲና መሰል ከሆኑ እንቅስቃሴዎች ባሻገር በአገር ውስጥ ትግሉን ለማደራጀት፣ ለማስተባበርም ሆነ ለማቀናጀት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ ድርጅቶች ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን

በማደራጀት ሆነ በማሰባሰብ በአገዛዙ ላይ የጋራ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በማድረግ፤ የውጭ አገር መንግሥታትም ሆኑ መንግሥስታዊ ያልሆኑ ሆነ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በአምባገነኑ አገዛዝ ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲያስተካክሉ የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ግምት ያለውና የሚመሰገን ሥራ ቢሆንም የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ከማስወገድ አንጻርም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያ ሥርዓትን እውን ከማድረግ አንጻር የሚኖረው ሚና ኢምንት ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም ነው በውጭ የሚገኙ የፖሊቲካ ድርጅቶች ከሚያከናውኑት ተግባር ሌላ አገር ውስጥ በህቡዕ ለሚደረጉ የማደራጀትና የመቀስቀስ ተግባሮች ከፍተኛው ትኩረት ሰጥተው ቢሰማሩ ትግሉ ፍሬያማ ሊሆን ይችላል የሚባለው።

የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ለማስወገድ አመች የሆነውን ማናቸውንም የትግል ስልት መጠቀሙ አግባብነት ያለው ነው። አምባገነን አገዛዝን ለማስወገድ በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል ስልቱ ሰላማዊ ይሁን ትጥቃዊ የሚወስነው የሚታገለው ሕዝብ እንጅ አምባገነኑ አገዛዝ ወይም ባዕዳን ኃይሎች ሊሆኑ አይችሉም። የትጥቅ ትግል የትግል ስልታችን እንዲሆን መርጠናል የሚሉት የፖለቲካ ኃይላት ግን ትግሉን ከመጀመራቸው በፊት መጀመሪያ መዘጋጀት እንዲሁም ትግሉ እንቅፋቶቹን በመቋቋም ውጤት ሊያመጣ ስለሚችልበት ሁኔታ መገምገም፤ ማሰብና ማቀድ ይኖርባቸዋል። በተደጋጋሚ ውጤት አልባ በመሆን የታወቀውን መንገድ መከተል ወይም ከማይሆን ክፍል ትብብርና እርዳታ መጠበቅና መመኘት ራስንም ሆነ ሌላውን ከማታለል በስተቀር የሚገኝ ትርፍ የለም። በመስክ ላይ ያለው ተግባራዊ የትግል እንቅስቃሴ ከፕሮፓጋንዳውና ከቅሰቀሳው በፊት ዜናና መረጃ ሆኖ ቢናገር ትግሉ በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር አግኝቶ የሚጠናከርበት ሁኔታ ከመፍጠሩ በላይ ያልተጨበጠው ምኞት እውን አለመሆኑን አውቆ ተስፋ ሊቆርጥ የሚችለውን ወገን ትግሉን እንዳይሸሽ ለማድረግ ያስቻላል።

በሀገራችን እስካሁን የተጠናከረ ኅብረት ተመስርቶ የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ ያልተቻለውም ከላይ በተዘረዘሩት የፖሊቲካ ድርጅቶች ውስጣዊ ድክመት ምክንያት መሆኑን መግለጽ ያስፈልጋል። ተደላድሎ በሥልጣን ኮርቻ ላይ የተቀመጠን አምባገነን አገዛዝ ከስሩ መንግሉ ለመጣልም ሆነ ከዚያ በኋላ ሰላማዊና የተረጋጋ የፖሊቲካ ሥ ርዓት እውን እንዲሆን ለማድረግ የኅብረት ትግል አስፈላጊና ወሳኝ ነው። በርካታና የተለያዩ አመለካከቶችና እምነቶች በኅብረተሰብ ውስጥ ስር ሰደው ባሉበት ሁኔታ ደግሞ የኅብረት ትግል አማራጭ የሌለው ነው። በአገሪቱ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ እምነት ከሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ኅብረት መመስረት የማይተሰብም በመሆኑ ህብረት መፍጠር ያልተቻለ ሲሆን የአንድነት ኃይሎች የሚባሉት ደግሞ ከላይ በተዘረዘሩት ውስጣዊ ድክመት ኅብረት ለመፍጠርም ሆነ የፈጠሯቸውን ኅብረቶች አጠናክረው አምገነን አገዛዝን ማስወገድ አልቻሉም። በወያኔ የሥልጣን ዘመን በርካታ ኅብረቶች የተፈጠሩ መሆናቸውና ጉልህ የሆኑ አዎንታዊ አስተዋጽዖችን ማድረጋቸው አጠያያቂ ባይሆንም ከላይ በተዘረዘሩት ድክመቶች የተነሳ ሲመሠረቱ ዒላማ ያደረጉትን ግብ ሳይመቱ ተዳክመው ፈራርሰዋል። ከላይ እንደጠቀስነው ሁሉ የኀበረት ትግሎች ፍሬያማ እንዲሆኑ የወያኔን አምባገነን አገዛዝ በሁለገብ የትግል ስልት ማስወገድ የሚለውን ቁርጥ ያለ ዓላማ ይዘው መነሳት አለባቸው። በምርጫ፣ በልምምጥ፣ በልመና፣ በአማላጅ፣ …ወዘተ ወያኔን እናሻሽላለን እናዳክማለን የሚለው በዓላማው ውስጥ ከተዛነቀ የኅብረት ትግል ይዳከማል። ሁለተኛ የኅብረት ትግል ዋና ግብ የወያኔን አምባገነን አገዛዝ ማስወገድ ከሆነ ኅብረቱን ሊመሰርቱ የሚችሉ ኃይሎች ይህንኑ ዓላማ ቀዳሚ አድርገው ትግላቸውን በተጨባጭ በአገር ውስጥ ማካሄድ አለባቸው። ኅብረት የሚፈጠረው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ወይም ደግሞ ኅብረት መፈጠሩን ለማብሰሪያ ሳይሆን ተጨባጭ ትግል ለማካሄድ ነው። ተጨባጭ ትግል በሌለበት ኅብረት ፈጠርን የሚሉ አካሎች የስም ኀበረቶች ከመሆናቸው ሌላ ህልውናቸውን እንደ ድርጅት ለመጠበቅ ሌላ ኅብረት ለመጥራት ሲሯሯጡ ተመልክተናል። በአገር ውስጥ ሕጋዊነትን አግኝተው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ዓላማቸው የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ እስከሆነ ድረስና አደረጃጀታቸውንም ለተለያዩ ትግሎች ምቹ አድርገው እስካስተካከሉ ድረስ ሕጋዊነትን ተነፍገው በህቡዕ ትግል ከሚያካሄዱት ጋር ትግላቸውን ሊያቀናጁ የሚችሉበት በርካታ መንገዶች ይኖራሉ። በተለያዩ

የትግል ስልቶች ተሰማርተናል በሚሉትና በሰላማዊ መንገድ ብቻ በሚታገሉ መካከልም በተግባር የሚደረግ ትብብርና ኅብረት ይኖራል። ኅብረት ውጤታማ የሚሆነው በተግባራዊ እንቅስቃሴ ትብብር ሲኖር ብቻ ነው።

ለ25 ዓመታት በላያችን ተዘፍዝፎ ሕዝባችንን እያሰቃየ ያለውን ዘረኛና ከፋፋይ ጸረ ሕዝብና ጸረ አንድነት የሆነውን አገዛዝ በተባበረ ትግል ገርስሰን ለመጣል ድከመቶቻችንን እናርም እንላለን። ድርጅታችን ኢሕአፓ የወያኔን አምባገነን ሥርዓት ለአንዴም ለሁሌም ለማስወገድ ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲፋፋምና ግቡን እንዲመታ የሚያካሄደውን፣ በአገር ውስጥ በተጨባጭ የሚያካሄደውን ትግልም አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን እየገለጸ በመስከ ላይ በተግባር ለሚደረግ ኅብረትና ትብብር ምን ጊዜም ዝግጁ መሆኑን አበክሮ ለማሳሰብና ለማሳወቅ ይፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ትግሉ ድሉን ይቀዳጃል
ጸረ-ወያኔ ትግላችን ይፋፋም !!